# የካፒታል ገበያ የቁጥጥር አሰራር ዳሰሳ

## መግቢያ

በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የቁጥጥር ማዕቀፍ ተቆጣጣሪ የሆነው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ፈቃድ ለሚሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ገበያዎች፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ፣ የግብይት መሰረተ ልማቶች እና ራሳቸውን በራሳቸው ለሚቆጣጠሩ ድርጅቶች የቁጥጥር አሰራር ስርዓት ከዚህ በኋላ ‘’የአሰራር ሥርዓት/ሰነድ’’ ተብሎ የሚጠራውን አውጥቷል። ይህ የአሰራር ሥርዓት ባለሥልጣኑ በካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳር ውስጥ የሚሳተፉ የተለያዩ አካላትን እንዴት እንደሚቆጣጠር የሚያብራራ ነው። ይህ ሥርዓት አዳዲስ ህጎችን የማይፈጥር ወይም አዳዲስ ህጋዊ ግዴታዎችን በራሱ የሚጥል እንዳልሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው። ይልቁንም ከነባር የህግ ሰነዶች የሚመነጩትን የቁጥጥር ግዴታዎች በተለይም የካፒታል ገበያ አዋጅ እና እሱን ለማስፈጸም የወጡትን የተለያዩ መመሪያዎች አፈጻጸም እና የቁጥጥር ሂደት የሚያብራራ ነው።

የአሰራር ሥርዓቱ ለተለያዩ የገበያ ተዋንያን ተፈፃሚ የሚሆን ሲሆን ተቆጣጣሪው የእነዚህን ተዋንያን በአጠቃላይ "ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት" ብሎ ይጠራቸዋል። እነዚህም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን (እንደ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላሎች፣ አከናዋኞች፣ የኢንቨስትመንት ባንኮች፣ የኢንቨስትመንት አማካሪዎች፣ እና ሌሎችን) ፣የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎችን፣ የተዛማጅ ውሎች ገበያዎችን፣ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያዎችን፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አሰቀማጭ፣ ክፍያ አጣሪ እና ፈጻሚ ኩባንያዎችን፣ የገበያ መሰረተ ልማቶችን እና ራሳቸውን በራሳቸው የሚቆጣጠሩ ድርጅቶችን ያካትታል። ይህም የተለያዩ አካላትን በመሸፈን፣የአሰራር ሥርዓቱ የተለያዩ የገበያ ተሳታፊዎች ልዩ ባህሪያት እና የአደጋ መገለጫዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ወጥነት ያለው የተዋሃደ የቁጥጥር ማዕቀፍ የሚያቋቁም ነው።

ተቆጣጣሪው የአሰራር ሥርዓቱ ከሁሉም የሚመለከታቸው የካፒታል ገበያ ህጎች፣ የኢትዮጵያ ህጎች እና የቁጥጥር ማዕቀፎች ጋር አብሮ መነበብ እንዳለበት አፅንዖት ሰጥቷል። ይህ ማለት ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት የአሰራር ሥርዓቱን ሰነድ ብቻ ሳይሆን እንደ ሁኔታው እና እንደ ጉዳዩ የንግድ ህግን፣ የኢንቨስትመንት አዋጅን እና የግል መረጃ ጥበቃ አዋጅን ጨምሮ የተለያዩ ተፈጻሚነት ያላቸው ህጎች መጠቀም አለባቸው ማለት ነው። እንዲሁም የአሰራር ሥርዓቱ ተቆጣጣሪው ተጨማሪ መረጃ ለመጠየቅ ወይም በተወሰኑ አካላት ላይ ከፍ ያሉ ደረጃዎችን ለመጫን ያለውን ስልጣን ከመጠቀም እንደማያግደው ያስቀምጣል። ይህ የቁጥጥር ተለዋዋጭነትን ከግምት ውስጥ ያስገባ እና ተቆጣጣሪው አሰራሩ ሲዘጋጅ ያልተጠበቁ ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ወይም ልዩ ሁኔታዎችን ምላሽ እንዲሰጥ የሚያስችል መሆኑን ለማሳየት የተቀመጠ ነው።

## የቁጥጥር አሰራር፡ የተቀናጀ የቁጥጥር ሞዴል

### ህግ ማስከበር ላይ የተመሰረተ የቁጥጥር አሰራር

ከሰነዱ መረዳት እንደሚቻለው ተቆጣጣሪው የቁጥጥር ሥራውን በተመለከተ በህግ ማስከበር ላይ የተመሰረተ የቁጥጥር አሰራር እና አደጋ ላይ የተመሰረተ የቁጥጥር አሰራር፣ የሁለቱን ድብልቅ የቁጥጥር አሰራር እንደሚጠቀም ተመልክቷል። ይህንን ድብልቅ ሞዴል መረዳት ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት ባለሥልጣኑ የቁጥጥር ተግባሮቹን እንዴት እንደሚያከናውን እንዲገነዘቡ የሚያግዝ ነው።

ህግ ማስከበር ላይ የተመሰረተ የቁጥጥር አሰራርን በተመለከተ ሁሉም ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት በተቆጣጣሪው መመሪያዎች ውስጥ በተቀመጡት የተወሰኑ መስፈርቶች መሠረት በተከታታይ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል። በዚህ አሰራር መሰረት ተቆጣጣሪው ሁሉም ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት ለአስተዳደር፣ ለፋይናንስ ጤናማነት እና ለግብይት አሰራር ዝቅተኛ የተቀመጡ መስፈርቶችን እንዲያከብሩእና እንዲያሟሉ ይጠብቃል። ሆኖም በአሰራሩ መሰረት በመመሪያዎቹ ውስጥ ያሉት ድንጋጌዎች አስገዳጅ እና ጥብቅ አለመሆናቸውን ይልቁንም አንዳንዶቹ ከሁኔታዎች ተለዋዋጭነት ጋር አማራጭ የሚሰጡ መሆናቸው ተመልክቷል።

ይህም ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት መሰረታዊ የቁጥጥር ዓላማዎችን እስካሳኩ ድረስ ከግብይት ሞዴሎቻቸው እና ሁኔታዎቻቸው ጋር የሚስማሙ አሰራር እና አቀራረቦችን እንዲከተሉ ይፈቅድላቸዋል።

በዚህ ሚዛናዊ አካሄድ መሰረት የተለያዩ መጠኖች፣ ችሎታዎች እና የአደጋ መገለጫዎች ላሏቸው ድርጅቶች አንድ አይነት የቁጥጥር ሞዴል ለሁሉም ተግባራዊ ማድረግ በማደግ ላይ ላለ የካፒታል ገበያ ተገቢ ላይሆን እንደሚችል መረዳት ይቻላል። በዚህ አሰራር ተቆጣጣሪው በመመሪያዎቹ የተመለከቱ ጥብቅ መስፈርቶችን ከተለዋዋጭ መስፈርቶች ጋር በማጣመር ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ እና ለመላመድም ቦታ እንዲኖራቸው ያደርጋል። ተቆጣጣሪው በዚህ መንገድ የገበያ ዕድገትን ሊያዘገዩ ወይም ሊያግዱ የሚችሉ አላስፈላጊ የቁጥጥር ሸክሞችን በማስወገድ ተገዢነት (ህግ ማስከበር) ያበረታታል።

## በአደጋ ላይ የተመሰረተ የቁጥጥር አሰራር

በአደጋ ላይ የተመሰረተ ቁጥጥር ተቆጣጣሪው ቁጥጥር በሚያደርግባቸው አካላት ሊከሰቱ የሚችሉ ውድቀቶችን አስቀድሞ እንዲገምት፣ ቀደም ብሎ እንዲያውቅ እና እንዲያስተዳድር የሚያስችል አካሄድን ይጠቀማል። ለሚከሰቱ ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ተቆጣጣሪው በአደጋ ላይ የተመሰረተ ቁጥጥር ተግባራዊ በማድረግ አደጋዎችን ቀድሞ እንዲለይ እና በግለሰብ አካላት እና በሰፊው የካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳር ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ የውድቀት ወይም ጥሰቶች ውጤቶችን እንዲገመግም ያስችለዋል።

የአሰራር ሥርዓቱ በአደጋ ላይ የተመሰረተ ቁጥጥርን በተመለከተ እንደተጋላጭነት ትንተና፣ የግብይት እና ሌሎች ሥርዓቶች ጥቃት የመቋቋም ብቃት ፍተሻ እና የአደጋ ክትትል ቴክኒኮች ያሉ የአደጋ ግምገማ ዘዴዎችን መተግበርን እንደሚያካትት ያስረዳል። እነዚህ ዘዴዎች ተቆጣጣሪው አሉታዊ ክስተቶችን የመከሰት እድል እና በስርዓቱ ላይ ያላቸውን ተጽዕኖ ለመለየት ይረዳሉ። ይህ የቁጥጥር አሰራር ቁጥጥር ለሚደረግባቸው አካላት ጉልህ አንድምታዎች ያሉት ሲሆን በዚህ አሰራር መሰረት በተለይ ከፍተኛ የአደጋ መገለጫዎች ያሏቸው ደርጅቶች፣ ወሳኝ ጠቀሜታ ያላቸው መሰረተ ልማቶች እና ውስብስብ ስራዎች ያላቸው አካላት ዝቅተኛ የአደጋ መገለጫዎች ካላቸው አካላት የበለጠ ከፍተኛ የቁጥጥር ትኩረት የሚሹ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

# የካፒታል ገበያ የቁጥጥር አሰራር ዳሰሳ

በኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ የቁጥጥር ማዕቀፍ ተቆጣጣሪ የሆነው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ፈቃድ ለሚሰጣቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ ገበያዎች፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ፣ የግብይት መሰረተ ልማቶች እና ራሳቸውን በራሳቸው ለሚቆጣጠሩ ድርጅቶች የቁጥጥር አሰራር ስርዓት ከዚህ በኋላ ''የአሰራር ሥርዓት/ሰነድ'' ተብሎ የሚጠራውን አውጥቷል፡፡ ይህ የአሰራር ሥርዓት ባለሥልጣኑ በካፒታል ገበያ ሥነ-ምህዳር ውስጥ የሚሳተፉ የተለያዩ አካላትን እንዴት እንደሚቆጣጠር የሚያብራራ ነው፡፡ ይህ ሥርዓት አዳዲስ ህጎችን የማይፈጥር ወይም አዳዲስ ህጋዊ ግዴታዎችን በራሱ የሚጥል እንዳልሆነ መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ ይልቁንም ከነባር የህግ ሰነዶች የሚመነጩትን የቁጥጥር ግዴታዎች በተለይም የካፒታል ገበያ አዋጅ እና እሱን ለማስፈጸም የወጡትን የተለያዩ መመሪያዎች አፈጻጸም እና የቁጥጥር ሂደት የሚያብራራ ነው፡፡

## የትብብር እና ግልጽነት አስፈላጊነት

በሰነዱ፣ በቁጥጥር ሥራ ግንኙነት ውስጥ የትብብር እና ግልጽነት አስፈላጊነትን ወሳኝ መሆኑን ባለሥልጣኑ አፅንዖት ሰጥቶ አሰቀምጧል፡፡ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት በቁጥጥር እና ክትትል ወቅት ክፍት እና ተባባሪ መሆን፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃ መስጠት፣ ተዛማጅ መዝገቦችን ማቅረብ እና ማመቻቸት እና ከተቆጣጣሪው ጋር መተባበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ ከተቆጣጣሪው የመተባበር ግዴታ መስፈርት ብቻ ሳይሆን ውጤታ ማቁጥጥር በተቆጣጣሪው እና ቁጥጥር በሚደረግባቸው አካላት መካከል ባለው መተማመን እና የጋራ ትብብር ላይ የተመሰረተ መሠረታዊ መርህ መሆኑን የሚያንጸባርቅ ነው፡፡

### የቁጥጥር ማዕቀፍ፡ በስራ ቦታ ላይ እና ከስራ ቦታ ውጭ የሚደረግ ቁጥጥር፣ ከስራ ቦታ ውጭ የሚደረግ ቁጥጥር (ቅኝት)፡

የተቆጣጣሪው የክትትል ማዕቀፍ በዋናነት በሁለት ዋና ዋና ዘዴዎች ላይ ያተኩራል፡፡ እነዚህም በስራ ቦታ ላይ በመገኘት የሚደረግ አስተዳደራዊ ምርመራ (ፍተሻ) እና ከስራ ቦታ ውጭ የሚደረግ ቁጥጥር (ቅኝት) ዘዴዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ዘዴዎች በጋራ ተግባራዊ ሲሆኑ አንዱ የሌላውን ዜዴ ክፍተት የሚሞሉ እና የሚደጋገፉ ሲሆኑ የእያንዳንዱን ቁጥጥር የሚደረግበት አካል አጠቃላይ ስራዎች፣ የፋይናንስ እና የተገዢነት ሁኔታ ለተቆጣጣሪው አጠቃላይ ምስል የሚሰጡ ናቸው፡፡

ከስራ ቦታ ውጭ የሚደረግ ቁጥጥር (ቅኝት)፣ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላትን ወደ ስራ ቦታቸው በመግባት አካላዊ ጉብኝቶችን ማድረግ ሳያስፈልግ በርቀት መከታተልን የሚያካትት ነው፡፡ ይህ የሚከናወነው አደጋዎችን ወይም ችግሮችን ቀደም ብለው ለመለየት ድርጅቶች የሚያቀርቧቸውን ሰነዶች እና መረጃዎች እንደ የቁጥጥር ሰነዶች፣ የፋይናንስ መግለጫዎች፣ መደበኛ ሪፖርቶች እና የገበያ ክትትል መረጃዎች በጥንቃቄ በማጥናት ነው፡፡ ተቆጣጣሪው እነዚህ የቀረቡ ሰነዶች ከቁጥጥር መስፈርቶች ጋር መጣጣማቸውን ለማረጋገጥ እና ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልጋቸው ሊሆኑ የሚችሉ አደጋዎችን ለመለየት ይገመግማል፡፡ ከስራ ቦታ ውጭ የሚደረግ ቁጥጥር (ቅኝት)፣ ቀደም ሲል ከተደረጉ ፍተሻዎች የተገኙ ግኝቶችን እና የአንድ ቁጥጥር የሚደረግበት አካል ቀጣይ አፈጻጸም እና የአደጋ ተጋላጭነት ግንዛቤዎችን ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ መረጃዎችን መገምገምን ያካትታል፡፡

ሌላው ከስራ ቦታ ውጭ የሚደረግ ቁጥጥር (ቅኝት) ለሁሉም ቁጥጥር ለሚደረግባቸው አካላት ቀጣይነት ያለው አፈጻጸም፣ የንግድ አሰራር፣ የአደጋ ተጋላጭነት እና የቁጥጥር መመሪያዎችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ማክበርን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመከታተል የሚደግፍ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ቀጣይነት ያለው ግምገማ ተቆጣጣሪው ቁጥጥር የሚያደርግባቸውን አካላት አዝማሚያዎችን ለመለየት፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የቁጥጥር ሥራዎችን ለመለየት ያስችለዋል፡፡ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት ከስራ ቦታ ውጭ በሚደረግ ቁጥጥር (ቅኝት) ግዴታዎቻቸው በየጊዜው ሪፖርቶችን በማቅረብ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን ትክክለኛ እና የተሟላ መዝገቦችን መያዝ እና ለተጨማሪ መረጃ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት መዘጋጀት አለባቸው፡፡

### በስራ ቦታ ላይ የሚደረግ ምርመራ (ፍተሻ)

በስራ ቦታ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር (ፍተሻ) ቁጥጥር የሚደረግባቸውን አካላት አሰራር በጥልቀት መገምገምን ያካትታል፡፡ ይህም ሥራቸውን፣ የአደጋ አስተዳደር፣ የሥራ አስተዳደር እና የተገዢነት(የህግ ማስከበር) እንቅስቃሴዎቻቸውን ይሸፍናል፡፡ እነዚህ ተግባራት ቁጥጥር ወደ ሚደረግባቸው አካላት ቢሮዎች አካላዊ ጉብኝቶችን ማድረግን ያካትታል፣ እነዚህም በቅድሚያ ማሳወቂያ ወይም ያለማሳወቂያ ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡ በስራ ቦታው ላይ የሚደረግ ቁጥጥር ዋንኛ ዓላማ የፋይናንስ መዝገቦችን እና የቀረቡ ሪፖርቶችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፣ የንግድ ሥራዎችን መገምገም እና የአደጋ ቅነሳ መቆጣጠሪያዎችን ውጤታማነት ማረጋገጥ ነው፡፡

በአሰራር ሥርዓቱ መሰረት በስራ ቦታ ላይ የሚደረግ ምርመራ ተግባራዊነት ጋር በተያያዘ ቀጠሮ በመስጠት የሚፈጸምበት አግባብ አንዱ አማራጭ ነው፡፡ ቁጥጥር የሚደረግበት አካል ስራ ቦታ ላይ ተቆጣጣሪው የምርመራ (ፍተሻ) ስራ ከመጀመሩ በፊት በሁለቱ አካላት መካከል በሚደረግ ውይይት እና በባለስልጠጣኑ ፈቃድ መሠረት ቁጥጥር የሚደረግበት አካል ተቆጣጣሪው የጉብኝቱን የጊዜ ሰሌዳ እንደገና እንዲይዝ ወይም እንዲቀየር ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም አስፈላጊ ሠራተኛ በምርመራው (ፍተሻ) ጊዜው ውስጥ ላይገኝ የሚችል ከሆነ፣ ቁጥጥር የሚደረግበት አካል ይህንኑ ለተቆጣጣሪው ማሳወቅ አለበት፡፡ ባለሥልጣኑ በቦታው ጉብኝት ከማጀመሩ በፊት፣ የቦታውን የምርመራ (ፍተሻ) ስራ የሚደግፉ እና መሟላት ያለባቸውን ሰነዶች እንዲቀርቡ ሊያዝ ይችላል፣ ቁጥጥር የሚደረግበትም አካል እነዚህን ሰነዶች በባለሥልጣኑ በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

ተቆጣጣሪው ምርመራ (ፍተሻ) በሚያደርግበት ወቅት ከራሱ ሰራተኞች በተጨማሪ፣ የህግ አስከባሪ መኮንኖችን፣ ኦዲተሮችን ወይም ራሱ ፈቃድ የሰጠውን ማንኛውንም አካል በመጠቀም ከስራ ቦታ ውጭ ቅኝት ወይም በስራ ቦታው ላይ ምርመራ (ፍተሻ) ማድረግ እንዲችል በአዋጁም ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት በባለሥልጣኑ ጥያቄ መሠረት ሁሉንም አስፈላጊ ሰነዶች እና መዝገቦች ለሚመለከተው መርማሪ ክፍት ማድረግ ወይም እንዲያገኝ ማመቻቸት አለባቸው፡፡ ይህ አሰራር ተቆጣጣሪው አካል የቁጥጥር ኃላፊነቶቹን በሚወጣበት ጊዜ ከሚቆጣጠራቸው አካላት ሙሉ ትብብር ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን የሚያጎላ ነው፡፡

# የካፒታል ገበያ የቁጥጥር አሰራር ዳሰሳ

## ሦስቱ የምርመራ ዓይነቶች

የአሰራር ሥርዓቱ ሦስት የተለያዩ የምርመራ (ፍተሻ) ምድቦችን ያስቀምጣል፣ እያንዳንዳቸው የተለየ ዓላማ ያላቸው እና በተለያዩ ሁኔታዎች የሚፈጸሙ ናቸው።
የመጀመሪያው፣ መደበኛ ምርመራ (ፍተሻ) ሲሆን የተገዢነት (የህግ ማስከበር) ምርመራዎችን ለማድረግ፣ የቀረቡ የፋይናንስ መዝገቦችን እና ሌሎች ሪፖርቶችን ትክክለኛነት ለመገምገም፣ የንግድ ሥራዎችን ለመፈተሽ፣ የአስተዳደር መዋቅርን እና አሰራርን ለመመርመር፣ አደጋን ለመቀነስ በቦታው ላይ ያሉትን የቁጥጥር ዘዴዎች ጥራት ለመገምገም እና ከአስተዳደር ጋር ለመተባበር በየጊዜው ቁጥጥር ወደ ሚደረግባቸው አካላት ቢሮዎች የሚደረግ የአካል ጉብኝት ነው። የመደበኛ ፍተሻዎች ድግግሞሽ እንደተቋሙ አይነት እና በስርዓት ጠቀሜታው ይለያያል።

ሁለተኛው፣ ድንገተኛ ምርመራ (ፍተሻ) ሲሆን በገበያ ተሳታፊ የተፈጸሙ ወይም የተጠረጠሩ ጥሰቶችን ለመመርመር የሚደረግ ቀጠሮ ያልተያዘ ለፍተሻ ነው። ይህ በኢንቨስተሮች የሚነሱ ቅሬታዎችን፣ የጠቋሚዎች ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ጉዳዮችን ለመፍታት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በተቆጣጣሪው አነሳሽነት የሚጀመር ነው። የድንገተኛ ፍተሻዎች ባህሪ ቁጥጥር የሚደረግባቸው አካላት በማንኛውም ጊዜ ለምርመራ ዝግጁ መሆን አለባቸው ማለት ነው።

ሦስተኛው፣ ታርጌት ምርመራ (ፍተሻ) ሲሆን በገበያ ውስጥ ወሳኝ ጉዳዮችን ወይም ለየት ያሉ አዝማሚያዎችን ጨምሮ ተቆጣጣሪው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የተወሰኑ ወይም ተጋላጭ ትኩረት የሚሹ ቦታዎችን ለመፍታት የታለመ ፍተሻ ነው። ይህ የምርመራ ዘዴ ሰፊ ቦታዎችን ከሚሸፍነው መደበኛ ምርመራ የተለየ ከመሆኑ ባሻገር የተወሰኑ አሳሳቢ ጉዳዮች በጥልቀት ለመዳሰስ የተነደፈ የፍተሻ ዘዴ ነው። ለምሳሌ፣ተቆጣጣሪው በተወሰነ አይነት የህግ ጥሰት ላይ አዝማሚያ ካየ ወይም በተወሰነ የስራ መስክ ላይ ተጋላጭነት መኖሩን ካወቀ፣ ዝርዝር መረጃ ለመሰብሰብ እና በገበያው ውስጥ ያለውን የችግሩን ስፋት ለመገምገም የታርጌት ፍተሻ ሊያካሂድ ይችላል።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት
Ethiopian Capital Market Administrative Tribunal
ECMAT